# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከልን በተመለከተ

## የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ዳሰሳ ሪፖርት

ሐምሌ 2002 ዓ.ም

# ማውጫ


**መግቢያ** ............ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት ............ 3

የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም ............ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት ............ 4

የዳሰሳ ኦዲቱ ዓላማ ............ 7

**በዳሰሳ ኦዲቱ የተገኘው ግኝት** ............ 7

**የኦዲት ቡድኑ አስተያየት** ............ 11

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ በአለማችን ካሉ ኋላ ቀር ከሆኑ ሀገሮች አንዷ ስትሆን ህዝቦቿም አብዛኛው በድህነት የሚኖሩና ለተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው፡፡ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ጎዳና ተዳዳሪነትን፣ ዝሙት አዳሪነትን፣ ቦዘኔነትን፣ ልመናንና የአልኮልና የአደገኛ ዕፆች ሱሰኝነትን ያጠቃልላሉ፡፡ ለማሕበራዊ ደሕንነት ችግሮች ዋነኛ ተጋላጭ የሆኑት ቤተሰብ፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ናቸው፡፡ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ለድህነት፣ ለህመም፣ ለበሽታ፣ ለልመናና ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡ የተለየ ትኩረት እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል፡፡

2. በ1987 ዓ.ም. የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/87 የማህበራዊ ችግሮችን የመከላከል ስራ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ ሲሆን፣ ይህንኑ አዋጅ መሰረት በማድረግ በ1989 ዓ.ም የማህበራዊ ደህንነት ልማት ፖሊሲ ወጥቷል፡፡ በፖሊሲው ላይም የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሰጥቷል፡-

   - የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማቃለል የሚያስችሉ በተለይ ገጠሩን መሰረት ያደረጉ የኢኮኖሚ የልማት እርምጃዎች እንደሚወሰድ፣ እንዲሁም የችግሮቹን መስፋፋት ለመገደብ የሚያስችሉ ህጎችና ደንቦች እየወጡ ተግባራዊ እንደሚሆኑ፣
   - በማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የተጠመዱትን ከሚገኙበት ችግር ለማላቀቅ የሚያስችሉ የተሀድሶ፣ የሙያ ስልጠና፣ እንዲሁም የስራ ስምሪት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች የሚዘረጉበት ሁኔታ እንደሚያመቻች፣
   - ገንቢ የሆኑትን ልማዶች ከማበረታታት ጎን ህብረተሰቡ ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መንስኤ ከሆኑት ጎጂ እምነቶች፣ ጎታች ልማዶችና አስተሳሰቦች እንዲላቀቅ ትምህርት የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲመቻች እንደሚያደርግ፣

- ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ ምርታማነትን የሚቀንሱ እንደ ቦዘኔት፣ ዝሙት አዳሪነት፣ በልመና ተዳዳሪነትና የመሳሰሉትን የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማቃለል የሚያስችሉ የልማት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች እየተቀየሱ ተግባራዊ እንደሚሆኑ፣
- የጎዳና ተዳዳሪነትንና ወጣት ጥፋተኝነትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማቃለል የሚያስችሉ የልማት ፕግራሞችና አገልግሎቶች እየተቀየሱ ተግባራዊ እንደሚሆኑ፣
- አካልና አዕምሮ የሚያደነዝዙ የአልኮልና የአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነትን፣ ስነ-ምግባርን የሚያጎድፉ ልማዶችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማቃለል የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንደሚወሰድ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም ህብረተሰቡ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማቃለል ለሚዘረጓቸው ፕሮግራሞች ድጋፍና እገዛ እንደሚደረግ፣

ተገልጿል፡፡

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ1997 ዓ.ም ባካሄደው የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት ላይ ደግሞ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የመከላከሉ ስራ ድንበር ዘለል በመሆኑ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ብቻ የሚሰራ ሳይሆን በሁሉም መንግስታዊ መ/ቤቶች ዕቅድ ውስጥ ተካቶ መስራት እንደሚገባው ውሳኔ ላይ መደረሱን፣ በዚህም መሠረት የማህበራዊ ችግሮችን የመከላከል ሥራ ኃላፊነት በ1987 ዓ.ም ከወጣው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አዋጅ ላይ እንዲወጣና ይህንን ስራ እንዲሰራ የተቋቋመው ቡድን እንዲታጠፍ መደረጉ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የሚመለከቱ ስራዎች በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከ1997 ዓ.ም. እስከ 2001 ዓ.ም. ሳይሰራ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ በድጋሚ በ2001 ዓ.ም ባደረገው የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት ላይ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የሚመለከተውን ስራ የሚሰራ ሌላ የፌዴራል መንግስት

አካል የሌለ መሆኑ ስለታወቀ፣ ይህንን ሥራ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መስራት እንዳለበት ታምኖበት የሚኒስቴር መ/ቤቱ አዲስ በአረቀቀው የማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንዲካተት ተደርጎ አዋጁን ለማውጣት በዝግጅት ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

## *የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት*

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ አሰራር ለውጥ (BPR) ጥናት ከማድረጉ በፊት አንድ ሚኒስትርና ለሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም የማህበራዊ ደህንነት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው፡፡ በማህበራዊ ደህንነት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ስር የተሀድሶ ጉዳይ መምሪያ፣ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ጉዳይ መምሪያ፣ የቤተሰብ ጉዳይ ቡድን እና የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ተዋቅረዋል፡፡

5. የመሰረታዊ አሰራር ለውጥ (BPR) ጥናት ከተደረገ በኋላ በተዘጋጀውና ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅት ባልጸደቀው ድርጅታዊ መዋቅር ደግሞ አንድ ሚኒስትርና ሁለት ሚኒስትር ዴኤታ እነሱም የማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ እንደሚኖሩት ተደርጎ የተዋቀረ ሲሆን፣ በማበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ስር የግዥና ፋይናንስ፣ የሰው ኃብት አስተዳደር፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር፣ የማህበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ ዳሬክቶሬቶች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡

## *የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም*

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራውን ለማካሄድ ከመንግሥት በጀት የሚመደብለት ሲሆን፣ ለማህበራዊ ደህንነት ዘርፍ የስራ ማስኬጃ በ1999፣ 2000 እና 2001 ዓ.ም ከመንግሥት የተመደበለት በጀት ብር 1,124,100፣ 1,177,497፣ 1,201,150 በቅደም ተከተል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ብር 1,089,565.87፣ 1,124,114.20 እና 1,122,973.21 ነው፡፡ የበጀት አጠቃቀሙ በመቶኛ ሲገለጽ 87.6%, 95.4% እና 93.3% ነው፡፡

## *የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት*

7. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 4/87 መሠረት ከዚህ የሚከተለው ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

    1. አሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ ሕጎች ያዘጋጃል፣ ሲፀድቁም በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
    2. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የሥራ ሁኔታ፣ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎችን ይወስናል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
    3. ስለሠራተኛና አሠሪ ማህበራት ምዝገባ መመሪያ ያወጣል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማህበራት ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
    4. የሕብረት ስምምነት ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍፃሜ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
    5. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፤
    6. ሥራ ፈላጊዎችና ክፍት የሥራ መደቦች ስለሚመዘገቡበት፣ ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኙበት መንገድ መመሪያ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ለውጭ ዜጎችና ዜግነት ለሌላቸውም ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤
    7. ስለሰው ኃይልና የሥራ ሥምሪት፣ ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሠሪና ሠራተኛን ስለሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤
    8. ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በባህል መስኮች ከወንዶች ጋር በእኩልነት እንዲሳተፉ በተለይ በትምህርት፣ በሥልጠናና በሥራ ከመንግሥት ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ያጠናል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

9. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕፃናትና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያጠናል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

10. አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች የሚረዱበትን እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ዘዴዎችን ያጠናል፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

11. የማሕበራዊ ኑሮ ጠንቆች የሚወገዱበትን መንገድ ያጠናል፣ ጠንቆቹን በማስወገድ ረገድ አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ አስፈላጊውንም ድጋፍ ይሰጣል፤

12. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብ ደህንነት ስለሚጠበቅበትና ለጋብቻ ሥርዓት ስለሚደረግ እንክብካቤ ጥናት ያካሂዳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

8. በ1997 ዓ.ም በመ/ቤቱ በተሰራው የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት አሰራሩን ለማሻሻል በቀረቡት የመፍትሄ ሀሳቦች (Recommendations) መሰረት አዋጁ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ.471/98 ላይ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ደህንነት ልማት አገልግሎትን አስመልክቶ ከዚህ በታች የተጠቀሰው ኃላፊነት ሲሰጠው የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ የነበረው ኃላፊነት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

1. የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲጠበቅ፣

   ሀ. ሠራተኞችና አሠሪዎች በማህበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

   ለ. በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሦስትዮሽ አሠራሮች እንዲለመድ ያደርጋል፤

   ሐ. የሥራ ክርክሮች በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሠራሮችን ይዘረጋል፤

2. የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤

3. ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ሊኖር የሚችለበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለውጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎትን ይቆጣጠራል፤

4. በአገሪቱ ውስጥ መደበኛ በሆነና መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራውና በሥራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይልና ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤

5. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማህበራት ይመዘግባል፤

6. ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማህበራትንና የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፣ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤

7. የዜጎች ማህበራዊ ደህንነት የሚጠበቁባቸውንና የሚሻሻሉባቸውን ዘዴዎች በተለይም፣

   ሀ. የቤተሰብ ደህንነት ስለሚጠበቅበትና ጋብቻ ስለሚጠናከርበት፣

   ለ. የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለሚችሉበት፣

   ሐ. አረጋዊያን እንክብካቤ ስለሚያገኙበትና ተሳትፎአቸው ሊጎለብት ስለሚችልበት፣ ሁኔታ ያጠናል፣ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## *የዳሰሳ ኦዲቱ ዓላማ*

9. የዳሰሳ ኦዲቱ ዓላማ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአገሪቱ በኀላ ሁኔታ እየታየና በአገሪቱ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ የመጣውን የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ችግርን መከላከልና በችግሩ ተጠቂ የሆኑ ዜጎችን መልሶ የማቋቋሙን ስራ ብቃት ባለው መንገድ ማከናወኑን እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሰራር እና በታሰበው መሠረት ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሣቦችን ለሥራ አመራሩ ለማቅረብ ነው፡፡

## በዳሰሳ ኦዲቱ የተገኘው ግኝት

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 4/87 የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የሚወገዱበትን መንገድ የማጥናት፣ የማስተባበርና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ለተሀድሶ ጉዳይ መምሪያ ተጠሪ የሆነ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ጉዳይ ቡድን በ1997 ዓ.ም. ተቋቁሞ ነበር፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ በተካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ (BPR) ጥናት ይህንን በተመለከተ ያለው ኃላፊነት እንዲወጣ በመደረጉ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የሚመለከቱ ስራዎች ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ ያልተሰሩ መሆኑን በመ/ቤቱ ውስጥ ካገኘናቸው መረጃዎች ለመረዳት ችለናል፡፡ በመሆኑም፤

- የማበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የተመለከቱ ስራዎች በመ/ቤቱ ስትራቴጂክ እቅድና አመታዊ እቅዶች ውስጥ አለመካተታቸው፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ እንዲሰራ ኃላፊነት የተሰጠውና በመ/ቤቱ መወዋቅር ላይ የሚታየው የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ቡድን ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ መታጠፍን፣

- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከል ለመቆጣጠርና ለማቃለል ለሚዘረጋቸው ፕሮግራሞች ድጋፍና እገዛ የሚያደርግ አካል አለመኖሩን፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች በአገሪቱ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የሚያሳዩ የጥናትና ምርምር ተግባሮች አለመከናወናቸው፣ የስታትስቲክስ መረጃዎች አለመኖራቸው፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ህጎችና መመሪያዎች አለመውጣታቸው፣
- በማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች የተጠቃውን የህብረተሰብ ክፍል ከሚገኝበት ችግር ለማላቀቅ የሚያስችሉ የተሀድሶ፣ የሙያ ስልጠና እንዲሁም የስራ ስምሪት አገልግሎቶች የሚያገኙበት ሁኔታ አለማመቻቸት፣
- ህብረተሰቡ ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች መንስኤ ከሆኑ ጎጂ እምነቶች፣ ጎታች ልማዶችና አስተሳሰቦች እንዲላቀቅ የሚያስችሉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲመቻቹ አለመደረጉ፣
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ የፌዴራል መንግስት አካል ሳይኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሥራ ማቆሙ ለችግሩ መጨመር ምክንያት መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ችግሮች መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

11. በ1997 ዓ.ም በተከናወነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሪፖርት ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ የተሰጠውን ኃላፊነት ማለትም የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በመከላከል፣ በማቃለልና መልሶ በማቋቋም ረገድ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ፕሮግራሞች ነድፎና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ያልሰራ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የቀረቡት፤

    - የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ ስያሜአቸው ችግሮቹን በመከላከልም ሆነ በችግሩ ውስጥ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች መልሶ በማቋቋም ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር (Derogatory) መሆኑ፤

- በችግሩ ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተለይተው የሚታዩ ሳይሆኑ በህጻናት፣ በሴቶች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያንና በመሳሰሉት ስራዎች ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸው፤
- የጽንሰ ሀሳብ ብዥታ መኖሩ፤
- አርቆና ሰፋ አድርጎ (Strategically) አለማሰብና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነድፎ ያለመተግበር፤
- የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ስራ ሁሉንም መ/ቤቶች የሚመለከት (cross cutting issue) ሆኖ ሳለ በአተገባበር ላይ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ደረጃ ግንዛቤ እንዲፈጠር (mainstream) አድርጎ በቅንጅት መስራት ያለመቻል፤
- በክፍሉ የተመደቡት ሰራተኞች በልማዳዊ ስራዎች መጠመድ፤
- በስራ መስኩ የተሰማሩ ባለሙያች ችግሩ ግዙፍና ሊቀረፍ የማይችል አድርገው በማሰብ ከስራ የመሸሽ እና በየጊዜው ሥራ የመልቀቅ ሁኔታ መኖሩ፣

ናቸው።

12. በዚህም ጥናት ሪፖርት ላይ እነዚህን ችግሮች ለማሻሻል የቀረቡት የመፍትሄ ሀሳቦች (Recommendations)፤

    1. በማህበራዊ ደህንነት ልማት ፖሊሲ ውስጥ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን ጉዳይ አስመልክቶ የሰፈረው ሀሳብ ራሱን ችሎ መቀመጡ ቀርቶ በመ/ቤቱ ውስጥ በሚሰሩ ሁሉም ተግባሮች ውስጥ ተካቶ እንደሚከናወን ሆኖ ቢሻሻል፤
    2. በአዋጅ ቁጥር 4/87 ላይ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ተጠቂዎችን ስራ በተመለከተ ለመ/ቤቱ የተሰጠው ኃላፊነት በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች ስራ ላይ ባተኮረ መልክ ማስተካከያ ቢደረግ፤
    3. የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ጉዳይ ቡድን ስራ ከሌሎቹ የማህበራዊ ደህንነት የስራ ክፍሎች ጋር ተካቶ መከናወን ስለሚችል ለዚህ ሥራ የተቋቋመው ቡድኑ እንዲታጠፍ ቢደረግ

የሚሉ ናቸው።

13. በመሆኑም ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች እና ከጥናቱ በኂላም በተሠጡ የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን የተመለከቱ ስራዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ ትኩረት ሳያገኙና ሳይሰሩ የቆዩበት ሁኔታ ታይቷል፡፡

ሆኖም በ2001 ዓ.ም በመ/ቤቱ በድጋሚ በተሠራው የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ ጥናት (BPR) ሪፖርት ላይ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሌላ የሚሰራ አካል የሌለ በመሆኑ እና በ1997 ዓ.ም. የነበረው አመለካከት ትክክል እንዳልነበረ በመረዳትና የዜጎች ማህበራዊ ደህንነት ከተባለ ማንኛውም ዜጋ ማህበራዊ ችግር ከደረሰበት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ደንበኛ መሆኑ በመግለጽ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮችን የሚመለከቱ ጉዳዮች እየተሻሻለ ባለው ፖሊሲ እና ረቂቅ አዋጅ ላይ በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

## የኦዲት አስተያየት

14. በአገሪቱ ብዛት ያለው የህብረተሰብ ክፍል ለማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ችግሮች ተጋላጭ የሆነ ሲሆን ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና አሳሳቢ እየሆነ የመጣበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በመሆኑም ችግሩ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጎበት መፍትሄ እንዲያገኝ ካልተደረገ ለችግሩ ተጋላጭ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ የአገሪቱ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይታመናል፡፡

15. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ ችግሮች የሚወገዱበትን መንገድ የማጥናት፣ የማስተባበርና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 4/87 የተሰጠው ቢሆንም ይህ ኃላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ለተሀድሶ ጉዳይ መምሪያ ተጠሪ የሆነ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች ጉዳይ ቡድን ከማቋቋም በስተቀር ለዚህ ተግባር ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በመከላከል፣ በማቃለልና መልሶ በማቋቋም ረገድ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ኘሮግራሞች ነድፎ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ያልሰራ መሆኑን በ1997 ዓ.ም. ከተከናወነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሪፖርት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

16. ከዚህም ሌላ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ የፌዴራል መንግሥት አካል ሳይኖር ወይም እንዲቋቋም ሳይደረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሥራ ማቆሙ እና ይህንን ተግባር የማከናወን ኃላፊነቱ ከአዋጅ እንዲወጣ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ለችግሩ መጨመር አንዱ ምክንያት መሆኑ ይታመናል፡፡

17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ ኃላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮም ሆነ ከኃላፊነቱ እንዲወጣ ከተደረገበት ከ1997 ጀምሮ እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆችን በተመለከተ በማህበራዊ ደህንነት ልማት ዘርፍም ሆነ በሌላ አካል ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት የተሰራበት ባለመሆኑ የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች በአገሪቱ ላይ ያስከተሉትን ተጽእኖ፣ የችግሩን ጥልቀትና ስፋት በተጨባጭ ማስረጃ ለመረዳትና የክዋኔ ኦዲቱን አካሂዶ ችግሩን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ

ሃሳቦችን ለሥራ አመራሩ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን የኦዲት ቡድኑ ለማግኘት ባለመቻሉ ሥራውን ለመቀጠል አልቻለም፡፡

18. ከዚህም በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2001 ዓ.ም. በድጋሚ እያካሄደ ባለው የአሠራር ለውጥ ጥናት (BPR) ላይ በዘርፉ በሚሰሩ ሥራዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶት ተጠንቶ በረቂቅ አዋጁም ላይ እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ የክዋኔ ኦዲቱ ሥራ ቢቀጥል ኦዲቱ የሚያስገኘው ውጤት አነስተኛ ስለሚሆን ስራው ለጊዜው ተቋርጦ ወደፊት የመሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ጥናቱ ተጠናቆ በዘርፉ ያለው ሥራ ከቀጠለ በኂላ የክዋኔ ኦዲቱ ቢሠራ የበለጠ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

19. በመጨረሻም በዳሰሳ ኦዲቱ ወቅት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡